# አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት
# Action For Development

***Enabling dryland communities to realize their potential***



# “ዉሀን ተደራሽ የማድረግ ብርቱ ጥረት”

አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት በደቡብ ኢትዮጲያ ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን የዳሰነች እና ሳላማጎ ወረዳዎች ለሚገኙ ከ12ሺ በላይ ነዋሪዎች የንጹህ መጠጥ ዉሀ እንዲያገኙ አስችሏል።

ከክርስቲያን ኤይድ ጋር በመተባበር የተተገበረዉ ይህ ፕሮጀክት በሁለቱ ወረዳዎች ዉስጥ በድርቅ ለተጎዱ ነዋሪዎች የአስቸኳይ ጊዜ ዉሀ አቅርቦት ተደራሽ ለማድረግ ያለመ ነዉ። በሁለቱ ወረዳዎች ዉስጥ የሚገኙ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የዉሀ እጥረት የነበረባቸዉና ለዉሀ ወለድ በሽታዎች የሰፋ ተጋላጭነት የነበራቸዉ ናቸዉ።

በፕሮጀክቱ በተተገበረዉ የምንጭ ዉሀ ማጎልበት ስራ ማህበረሰቡ ለቤት ዉስጥ ግልጋሎቶች ንጹህ እና በቂ ዉሀን ለመኖሪያዉ በቀረበ ሁኔታ አግኝተዋል። ይህ የዉሀ ፕሮጀክት የዉሀ ወለድ በሽታዎች እንዲቀንሱ እና ዉሀ ለመቅዳት ረጅም መንገድ በመጓዝ ዉስጥ ያለዉን እንግልት ማቅለል ችሏል። ከዚህም ባለፈ የማህበረሰቡን ንጹህ እና በቂ ዉሀ የማግኘት መብት እንዲጠበቅ የላቀ አስተዋፅኦ አድርጓል።

**Action For Development (ETH)**
P.O.BOX 19859, Tel +251-011-662-59-76
afdethiopia@gmail.com info@afdethiopia.org www.afdethiopia.org